# የደመወዝ ጭማሪው የሀገሪቱ ዕድገት ውጤት ነው!

**ግርማ ፍቃዱ** 07/09/14

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ከአንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን በላይ ለሚሆነው የመንግሥት ሠራተኛ የስራና የኑሮው ሁኔታ እንዲሻሻል በማሰብ የመንግሥትን የመክፈል አቅም ያገናዘበ እንዲሁም ኢኮኖሚው ተረጋግቶ እንዲቀጥልና የዋጋ ንረትን በማይቀሰቅስ ሁኔታ ከሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የደመወዝ ጭማሪ እንደሚደረግ በቅርቡ ማስታወቃቸው አይዘነጋም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መንግሥት ከሚያስገነባቸው የቁጠባ ኮንደሚኒየም ቤቶች 20 በመቶ ዕጣ ለመንግስት ሰራተኞች ለብቻቸው እንደሚወጣ እንዲሁም በማኅበር ተደራጅተው ቤት ለመገንባት ለሚፈልጉ መሬት ተዘጋጅቶ እንደሚሰጣቸው ብሎም በአዲስ አበባ ከተማ የሚሠሩ የፌዴራልና የመዲናዋ የመንግሥት ሠራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት እንደሚመቻችላቸው ይፋ አድርገዋል፡፡

እርግጥ ይህ መንግስት ለሰራተኞቹ የሚያደርገው የደመወዝ ጭማሪና በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተጠቀሱት የማትጊያ ጥቅማ ጥቅሞች፣ በመንግስት ተነድፈው የተሻለና ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የተዘጋጁት የሪፎርምና የለውጥ ፕሮግራሞች ካለፉት ጊዜያት በተሻለ መንገድ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ። ከዚህ ባሻገርም ይበልጥ ተነሳሽነት ያለው፣ ልማታዊና የህዝብ አገልጋይነት መንፈሱ የዳበረ እንዲሁም ዴሞክራሲያዊ አመለካከቱና የሥራ ባህሉ የጐለበተ፣ ብቁና አስተማማኝ ክህሎት ያለው፣ በሥነ ምግባር የታነፀ የመንግስት ሰራተኛ ለመገንባት ያለው ሚና ቀላል አይደለም።

ታዲያ እዚህ ላይ 'ይህን ውጤት ለማምጣት መንግስት የሚያደርገው የደመወዝ ጭማሪና የማትጊያ ጥቅማ ጥቅሞች ምንጫቸው ምንድነው?' የሚል ጥያቄን ማንሳት ያስፈልጋል። ግና ጥያቄውን ለመመለስ መነሻ የምናደርገው ዓለማቀፋዊ ነባራዊ ሁኔታን ነው። ይኸውም የማንኛውም ሀገር መንግስት በሚያስመዘግበው ዕድገት መጠን የዜጎቹን የኑሮ ሁኔታ ደረጃ በደረጃ የሚያሻሽል መሆኑን ነው። እናም ከዚህ ዕውነታ በመነሳት የሀገራችን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስት ባለፉት አስር ተከታታይ ዓመታት በአማካይ የ11 በመቶ ዕድገት አስመዝግቧል። በዚህም በዓለማችን ላይ ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት በማስመዝገብ

ተጠቃሽና ለሌሎች ሀገራትም አርአያ መሆን ችሏል። ይህም መላው የሀገሪቱ ዜጎች ከተገኘው ልማት በየደረጃው ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። የመንግስት ሰራተኛውም የዚህ ጥቅም ተጋሪ ነው። እናም ጠቅላይ ሚኒስትር ኃ/ማርያም ደሳለኝ ይፋ ያደረጉት የደመወዝ ጭማሪና የማትጊያ ጥቅማ ጥቅሞች ሀገሪቱ ባለፉት አስር ዓመታት ያስመዘገበችው ዕድገት ውጤት መሆኑን ለመገንዘብ የሚያዳግት አይመስለኝም። ታዲያ ይህን የሀገራችንን ሁሉን አቀፍ ልማታዊ ዕድገት መረዳት፣ ዕድገቱ ምን ያህል ለዜጎች ሁለንተናዊ ለውጥ አስተዋፅኦ እያደረገ መሆኑን እንድንገነዘብ ያስችለናል።

## የልማት ዕድገቱ ዳራ

እንደሚታወቀው ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት የሀገራችንን ኢኮኖሚ ስር ከሰደደ ድህነትና ኋላቀርነት ለማላቀቅ እንዲሁም የህዝቡን ኑሮ ደረጃ በደረጃ ለማሻሻል የሚያስችሉ በርካታ የኢኮኖሚ ማህበራዊ የልማት ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ተቀርፀው ስራ ላይ ውለዋል፡፡ ውጤታቸው ስኬታማ እንደነበርም ከዛሬ ሃያ ሁለት ዓመታት በፊት የነበረችውንና የዛሬዋን ኢትዮጵያ በማየት መመስከር ይቻላል–"ማየት ማመን ነው" እንዲል ብሂሉ። እናም በዚህ ፅሑፍ ላይ የሀገራችንን ያለፉት አስር ዓመታትን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በጥቂቱም ቢሆን ለውድ አንባቢዎቼ ለማስቃኘት እሞክራለሁ።

ይሁንና የሀገራችን ምጣኔ ሀብት እመርታ ባለፉት አስር ዓመታት የነበረውን ጉዞና ውጤቱን ለመዳሰስ፣ ቀደም ሲል የነበረውን የአስር ዓመት ሂደት በጥቂቱ ማንሳት የግድ ይላል፡፡ ለምን? ቢሉ የኋላኛው አስር ዓመት ለአሁኑ ውጤታማ ጉዞ የራሱ የሆነ የማይተካ አስተዋጽኦ ስለነበረው ነው።

አምባገነኑና የዕዝ ኢኮኖሚ መርህን የሚከተለው የደርግ ሥርዓት ከመውደቁ በፊት የሀገራችን ምጣኔ ሀብታዊ አሃዝ ከዜሮ በታች እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም። ሥርዓቱ ከወደቀ በኋላ ያንን የደቀቀ ኢኮኖሚ ለማቃናት ከባድ መስዋዕትነት እንደሚጠይቅ ቀድሞ የተተነበየ ነበረ፡፡ እናም ተራራ የሚያክለውን የሀገሪቱን ድህነት ለመዋጋት ሶስት መርሆዎች ተቀየሱ፡፡ በመጀመሪያው አስር ዓመት መንግስትና ህዝብ የተጓዙባቸው መንገዶች በሀገሪቱ ለረጅም ጊዜ የተንሰራፋውን ድህነት ለማሸነፍ ፈጣን ባለመሆናቸው፣ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እንዲሁም ሁሉንም ዜጋ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርግ

የዕድገትና ድህነትን የማስወገድ መርህ መዘርጋት አማራጭ የሌለው ብቸኛ መፍትሔ ነበር፡፡

ከ1984 ዓ.ም እስከ 1993 ዓ.ም ድረስ ባለው አስር ዓመት ውስጥ የፈራረሱና ያረጁ የኢኮኖሚ ማህበራዊ ተቋማትን ለማደስ፣ ኢኮኖሚውን ከኋሊት በማላቀቅ ወደ ፊት ለመመልከትና ትክክለኛ አቅጣጫን እንዲይዝ ለማድረግ የተደረጉት እንቅስቃሴዎች ቀላል አልነበሩም፡፡ በእነዚህ ዓመታት በዋነኛነት የመንግስት አስተዳደርንና ሀገሪቱ የምትመራባቸውን ተቋማት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ያልተማከሉ የማድረግ፣ ኢኮኖሚውን ከዕዝ ወደ ገበያ መር ስርዓት የማምጣት፣ በፖሊሲ መዛባት በጦርነትና በተፈጥሮዊ ክስተቶች ሳቢያ የተሽመደመደው ኢኮኖሚ አቅጣጫ እንዲቀየር የማድረግ ሰፊ ጥረት ተደርጓል፡፡ የቅድመ- ኢኮኖሚ ማሻሻያ ከነበረው ከ1984 እስከ 1993 ዓ.ም ድረስ ከደርግ ስልጣኑን የተረከበው የሽግግር መንግስቱ፤ ሰላምና መረጋጋትን ከማምጣትና የመንግስት አስተዳደራዊና መዋቅራዊ ማሻሻያዎችን ከማድረግ ባሻገር፤ የመካከለኛ ዘመን የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ በማድረግ ዘላቂ ልማት ለማምጣት ሰፊ ርብርብ ማድረጉ አይዘነጋም፡፡ በዚሁ ወቅት የተከናወኑ ተከታታይ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሞች በአራት መሰረታዊ መርሆች ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው፡፡

የመጀመሪያው በፖሊሲ መዛባት፣ በጦርነትና ተፈጥራዊ ክስተቶች ሳቢያ የተሽመደመደውን ኢኮኖሚ እንዲያሰራራ ማድረግ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የነበረውን የዕዝ ኢኮኖሚ አሰራሩንና የተሳሳቱ ፖሊሲዎች ውጤት የሆነውን የማክሮ ኢኮኖሚ አለመረጋጋት የማስተካከል ብሎም የሁለት አስተሳሰብ አደላደልና አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳደሩ ማነቆዎችን ደረጃ በደረጃ ለመቅረፍ በኢኮኖሚ ዕድገቱ ምቹ ሁኔታን መፍጠር የሚል ነው፡፡ ሶስተኛው ድህነት ለመቅረፍ የሚያስችሉ የሰው ሃይልና መሰረተ ልማትን በማጎልበት የተፈጥሮ ሃብት አያያዝንና አጠቃቀምን ማሻሻያ ፕሮግራሞች ማካሄድ ነው። አራተኛው ደግሞ ለኢኮኖሚ ፖሊሲው ተግባራዊነትና ለልማት ፕሮግራሞች ውጤታማነት የሚረዱ አስተዳደራዊ የማሻሻያ እርምጃዎችን መውሰድ ነበር፡፡

ከ1984 እስከ 1993 ዓ.ም ድረስ ስራ ላይ በዋሉ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን መሰረት በማድረግ ኢኮኖሚው በብዙ መልኩ መጠነኛ ዕድገት ማስመዝገብ ችሏል፡፡ በዚሁ በተጠቀሰው በአስር ዓመት ውስጥ የሀገር ውስጥ ምርት በቋሚ ዋጋ (Real GDP) ከ10 ነጥብ 5 ቢሊዮን ወደ 17 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር በመጨመር፤ የ5 ነጥብ 1 በመቶ ዓመታዊ

አማካይ ዕድገት ማሳየት የቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ይህም ከሀገሪቱ የህዝብ ቁጥር ዕድገት የበለጠ በመሆኑ፣ ዕድገቱ የነፍስ ወከፍ ገቢ እንዲጨምር አድርጓል፡፡ ይሁንና ይህ ዕድገት ቀደም ሲል ከተመዘገበው ሁለት በመቶ ዓመታዊ ዕድገት ጋር ሲነጻጸር የተሻለ ቢሆንም፣ ከዓመት ዓመት የሚዋዥቅበትና በተፈለገው መጠን ያደገ ነበር ለማለት ግን ማለት አይቻልም፡፡

በዚህ ወቅት ለሀገር ውስጥ ምርት በታየው ዕድገትና የገቢ ዕቃዎች አቅርቦት መሻሻል የተነሳ በ1983 ዓ.ም መጨረሻ ሃያ አንድ በመቶ የነበረውን የዋጋ ግሽበት ከ1984 እስከ 1993 ዓ.ም በአማካይ ወደ ስድስት በመቶ ለማውረድ ተችሏል፡፡ እነዚህ ትግበራዎችም ኢኮኖሚው ከገጠመው የከፋ የኋሊት ጉዞ ለመውጣት የረዱና መጠነኛ ዕድገት ያስመዘገቡ ቢሆንም፣ ዜጎችን ከዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ከመውጣት እንዲሁም የምርት ዓመቱን ግብ ከማሳካት አኳያ አመርቂ ውጤት ተመዝግቧል ለማለት ግን የሚያስደፍር አልነበረም፡፡ በመሆኑም ከ1994 ዓ.ም በፊት መንግስት ሲከተለው የነበረው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያና ትግበራ መለወጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የድህረ ማሻሻያ የአኮኖሚ ፖሊሲ ተቀርፆ ተግባር ላይ ማዋል የግድ ነበር፡፡

የድህረ - ማሻሻያ የአኮኖሚ ፖሊሲው ከ1994 እስከ 2005 ዓ.ም ድረስ ያመጣው ምጣኔያዊ ሀብት መጠን ፈጣንና ተከታታይ የለውጥ ዕድገት ያስመዘገበ ነበር፡፡ እናም ተግባራዊ በተደረገው በድህረ ማሻሻያ የኢኮኖሚና ፕሮግራም የአማካኝነት ለውጡ ፈጣንና ተከታታይ ሊሆን የቻለበት ምክንያት፣ ለዕድገቱ ግስጋሴ የተቀየሱ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ታዲያ ይህ የድህረ ማሻሻያው ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ማሻሻያ መንግስት በህዝብ ዘንድ እንዲሰርፁ ያከናወናቸው ዘመቻ ቃላል አልነበረም፡፡ በመሆኑም በ1994 እና በ1995 ዓ.ም ሰፋፊ መድረኮች በማካሄድ የድህረ ማሻሻያ ፖሊሲና ስትራቴጂው ወደ ትግበራ የገባበት ሁኔታ የነበረ ቢሆንም ቅሉ፣ በወቅቱ አዲስና የተሟላ ዝግጅት ባለመደረጉ ምክንያት ብሎም በ1995 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ በተከሰተው የተፈጥሮ ድርቅ አደጋ የተጠበቀውን ያህል ዕድገት ሊመዘገብ አልቻለም፡፡

እርግጥ የሀገራችን ፈጣንና የተከታታይ የልማት ዕድገት እየተመዘገበ የመጣው ከዚህ በኋላ ነበር፡፡ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ የተሟላ ዝግጅት በመደረጉና ህዝቡም መንግስት የቀረጻቸውን ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ በማድረጉ ኢኮኖሚያዊ ዕድገቱ ወደ ተሻለ እመርታ ለመሸጋገር በቅቷል፡፡ ላለፉት ዘጠኝ ዓመታትም መንግስት ልማታዊ የግል

ኢንቨስትመንቶችን በማበረታታትና የኪራይ ሰብሳቢነት አማራጮችን በማጥናት ለማስወገድ በመሞከርና በግሉ ዘርፍ የማይሰሩ የልማት ክንዋኔዎችን በመስራት፣ ያሉትን ውስን ሀብቶች መሠረታዊ ችግሮችን በሚፈቱበት የልማት ስራዎች ላይ በማዋል፣ የልማት ኃይሎችን በማቀናጀትና በመምራት፣ የህዝብ ተሳትፎን በማጎልበት እና የግል ኢንቨስትመንት በማበረታታት ፈጣን ቀጣይነትና ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ዕድገትና ማህበራዊ ልማት ለማምጣት ተችሏል፡፡

በድህረ- ማሻሻያው በተቀረፁ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን መሰረት በማድረግም ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ተከታታይነት ያላቸው የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሞች ስራ ላይ ውለዋል፡፡ የመጀመሪያው "የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም" በመባል የሚታወቅ ሲሆን፤ ይኸም ከ1995 ዓ.ም እስከ 1997 ዓ.ም ድረስ ተግባራዊ የተደረገ ፕሮግራም ነው፡፡ ቀደም ሲል የተከናወኑት የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሞች አፈጻጸማቸው ከተገመገሙ በኋላም፤ ከ1998 ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ የቆየውና "ፈጣንና ቀጣይነት ያለው" የተሰኘው ሁለተኛው የድህነት ቅነሳ የልማት ዕቅድ ገቢራዊ ሆኗል፡፡ እነዚህ ሁለት የድህነት ቅነሳ የልማት ፕሮግራሞች ፈጣንና ተከታታይ የልማት ዕድገት በማስመዝገቡ ሂደት የነበራቸው ሚና ከፍተኛ ነበር፡፡

እርግጥ የልማት ፕሮግራሞቹ ሀገሪቱን ከድህነት ለማላቀቅ እንደሚረዱ ታምኖባቸው በዚህም ከቀበሌ እስከ ሀገር አቀፍ ድረስ ህብረተሰቡን እንዲሁም በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ያሉትን የልማት አጋሮች ለማሳተፍ በሚያስችል መልኩ የተቀረፁ ነበሩ፡፡ እያንዳንዱ የልማት ዕቅድም ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ነባራዊ ሁኔታዎችን ብሎም የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ የተቀየሱ በመሆናቸው የየራሳቸው መሰረታዊ የትኩረት አቅጣጫ ያላቸው እንደነበር አይዘነጋም፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ ሳይጠቀስ የማይታለፈው ጉዳይ፤ እነዚህ የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሞች አንደኛው ከሌላኛው በአፈጻጸም ረገድ ከፍተኛ ተሞክሮ የተወሰደባቸው መሆናቸው ነው፡፡ አዎ! ሁለተኛው የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም ከመጀመሪያው እንዲሁም ሶስተኛው የድህነት ቅነሳ (ማለትም የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ) ሁለቱንም ፕሮግራሞች መነሻ በማድረግ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ከ1994 ዓ.ም እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ስራ ላይ የዋሉትን የመንግስት ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን በመተግበር አመርቂ የሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት ተመዝግቧል፡፡ በዚህ ወቅት በአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት በቋሚ ዋጋ በ1984 ከነበረበት 10 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር

በ2004 ዓ.ም ወደ 506 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ለማደግ ችሏል፡፡ በዚህም ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 11 ዓመታት የሀገራችን ኢኮኖሚ በአማካይ የ11 በመቶ ዕድገት እያስመዘገበ መጥቷል፡፡ ይህን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስገራሚ የሚያደርገው የዓለም ኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ በገባበት ወቅት የተመዘገበ ከመሆኑም በላይ፤ ሀገራችን በቅርብ ዓመታት ወዲህ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ ከሰሃራ በታች ከሚገኙ በዳጅ ከሌላቸው ሀገሮች ጋር ሲነፃፀር የላቀ መሆኑም ጭምር ነው፡፡

ይህ የሀገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት መጠን ትልቅ የገበያ ምንጭ ስለሆነና በተፈጠረውም አመቺ የኢንቨስትመንት ሁኔታ ተበረታትተው በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ባለሃብቶች በተለያዩ ዘርፎች እንዲንቀሳቀሱ አስችሏቸዋል፡፡ የተጀመረው ዕድገት በዚሁ ከቀጠለ ሀገራችን በቅርብ ዓመታት ከአፍሪካ በኢኮኖሚ ታላቅነቷን ልታስመሰክር እንደምትችል መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

## ፈጣንና ተከታታይ ለውጥ

ባለፉት አስር ዓመታት የሀገራችን አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት በአሜሪካን ዶላር በ1993 ዓ.ም ከነበረበት የስምንት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ወደ ሃያ ዘጠኝ ነጥብ ሰሶት ቢሊዮን አድጓል፡፡ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከሰሃራ በታች ካሉ ሀገሮችና ከዓለም ኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ሲነጻጸር ሀገራችን ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ መሰረታዊ የሆነ ለውጥ በማምጣት ላይ ትገኛለች፡፡ የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት ከዓለም አማካይ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ሲነጻጸር የተሻለ ሲሆን፤ በተለይም የዓለም ኢኮኖሚ በ2002 ከዜሮ በታች ዕድገት ሲያስመዘግብ፤ ሀገራችን ግን የላቀ የኢኮኖሚ ዕድገት አፈጻጸም ነበራት፡፡ ታዲያ ይህ ድል የተገኘው ሀገራችን የነደፈቻቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ውጤታማ በመሆናቸው እንደሆነ ከማንም የተሰወረ አይደለም፡፡

ከ1994 ዓ.ም በፊት የተከናወኑ የኢኮኖሚ መዋቅር ማስተካከያና ማሻሻያ ፕሮግራሞች የምጣኔ ሃብት እንቅስቃሴውን ከማነቃቃታቸው ባሻገር፤ የኋሊት ሲጓዝ የነበረውን የኢኮኖሚ ዕድገት ትክክለኛ አቅጣጫውን ይዞ እንዲጓዝ ያደረጉ መሆናቸውን እየተመዘገቡ ካሉት ዘርፈ ብዙ ፈጣንና ተከታታይ ዕድገቶች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ለፈጣንና ቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገት የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ መኖር ወሳኝ መሆኑ ስለታመነበት፤ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ የፊስካልና የሞኒተሪንግ ፖሊሲዎችን በማጣጣም እንዲሁም ዝቅተኛ

የመንግስት በጀት ጉድለትንና የውጪ አሸፋፈን እንዲኖር በማድረግ ብሎም የገንዘብ እንቅስቃሴው ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ዋጋ ዓመታዊ ዕድገት ጋር የተዛመደ እንዲሆንና የውጭ ምንዛሬ ምጣኔዎችን ለማስተካከል ያለሰለሰ ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህም ውጤት ተገኝቷል።

ባለፉት አስር ዓመታት ለሁለት ዓበይት የኢኮኖሚ ዘርፎች (ለግብርና እና ለኢንዱስትሪ) ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የአርሶና የአርብቶ አደሩን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ፣ የግሉ ዘርፍም በግብርና እና በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፎች እንዲሳተፍ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ሀገራዊ ምርትን ለማሳደግ መቻሉን ነው– በእስከ አሁኑ የተመዘገበው መረጃ የሚያስረዳው፡፡ በድህረ - ማሻሻያ ፕሮግራሙ ለመሰረተ ልማት ግንባታና ለስራው የሰው ሃይል ልማት በመንግስት የተሰጠው ትኩረት የላቀ በመሆኑ የተገኙ ውጤቶችም አበረታች ሆነዋል፡፡ እርግጥም በመንገድ ግንባታ፣ በኤሌትሪክ ሃይልና በቴሌኮሙኒኬሽን እንዲሁም በንጹህ ውኃ አቅርቦት ረገድ የተገኘው መሻሻል አገልግሎቶቹን ለማስፋፋት የጠየቁት ከፍተኛ የፋይናንስና የሙያ ክህሎቶች፤ የተፈራውን ያህል ስራዎቹን ሊያስተጓጉሏቸው አለመቻላቸውን የተገኙት ውጤቶችን አይቶ መመስከር የሚቻል ይመስለኛል፡፡

ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ የኢኮኖሚ ዕመርታችን የሁለት አሃዝ ዕድገት በማስመዘገቡ ሀገራችን በኢኮኖሚ ዕድገት ጎዳና በአፍሪካ ከሚገኙ ሶስት ሀገራት ግንባር ቀደም በመሆን ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት ለማስመዝገብ በቅታለች፡፡ የተገኘው የኢኮኖሚ ዕድገትም ከድህነት ወለል በታች የሚገኘው የህብረተሰብ ክፍል ቁጥር እንዲቀንስና በየደረጃውም ተጠቃሚ እንዲሆን ያስቻለ ነው፡፡

እናም በእነዚህ ዓመታት ውስጥ መንግስት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በገበያ ተኮር ሥርዓት እንዲራመድ በማድረግ፣ ዕድገቱ ቀጣይና ተከታታይ እንዲሆን ብሎም የህብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል የቻለ ቢሆንም፤ በቀጣዩ በአምስት ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካትና የዕድገቱ ቀጣይነት ለማረጋገጥ ትኩረት ተሰጥቶ መተግበር ከጀመረ ሶስት ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ በልማት ዕቅዱ ዓመታትም በገጠርም ሆነ በከተማ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ሀገሪቱ እያስመዘገበችው ካለው ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ተጠቃሚ በመሆን የነብስ ወከፍ ገቢያቸው እንዲያሳድጉ አስችሏቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሚሊዮነር ባለሃብቶች ቁጥር እያደገ መጥቷል፡፡

የሀገሪቱ የግብርና መር ፖሊሲ ወደ ኢንዱስትሪ መር በሂደት እንዲሸጋገር እየተደረገ ያለው ጥረትም የሚደነቅ ነው፡፡ ባለፉት አስር ዓመታት መንግስትና ህዝብ በጋራ በመሆን ባከናወኑት ሰፊ ጥረት እያስመዘገቡ ያሉት ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት አሁንም ግለቱን ጠብቆ በመካሄድ ላይ ነው፡፡ በዚህም ሀገራችን የቀየሰችውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የሦስት ዓመቱ አፈጻጸም አበረታታች በሚባል ደረጃ እየተከናወነ ነው፡፡ በልማት ዕቅዱ ሶስት ዓመታት በርካታ የመሰረተ ልማት ስራዎች በመከናወን ላይ ሲሆኑ፤ በከተሞች በአነስተኛና ጥቃቅን ዘርፎች ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር የተደረጉት ጥረቶች በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ልማታዊ የኢኮኖሚ አውታሩ ፈጣን ልማትን የማረጋገጥና ህዝብን በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እያደረገ ነው፡፡ በዚህም በሶስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ብቻ በሀገር አቀፍ ደረጃ በአነስተኛና ጥቃቅን የተሰማሩ 4 ነጥብ 1 ሚሊዮን ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር አስችሏል፡፡ በሀገሪቱ ገጠራማ ክፍልም አርሶ አደሩ እያካሄደ ያለውን ምርትና ምርታማነት የማሳደግ እንቅስቃሴ በእጅጉ ውጤታማ በመሆኑ፤ ሞዴል ሚሊዮነር አርሶ አደሮች እንዲፈጠሩ አድርጓል፡፡ ይህ ደግሞ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ እየተደረገ ያለውን ሽግግር የሚያፋጥን መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡

ሀገራችን በአሁኑ ወቅት መጠነ ሰፊ በሆነ መልኩ በገጠርም ሆነ በከተማ የምታከናውነው የልማት ርብርብ የህብረተሰቡ የኑሮ ደረጃ እንዲቀየር ማድረጉ የማይካድ ሃቅ ነው፡፡ እናም አብዛኛዎቹ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች እንደሚተነትኑት ፈጣንና ተከታታይ ዕድገቱ በዚሁ ከቀጠለ በቀሚቀጥሉት አስራ አምስት ዓመታት ውስጥ ሀገሪቱ ባስቀመጠችው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መካከለኛ ገቢ ካላቸው ጎራ ለመሰለፍ ያስችላታል፡፡

ዕድገቱ የዜጎችን የትምህርት፣ የጤናና የንፁህ መጠጥ ውኃ ...ወዘተ ተጠቃሚነት የመሳሰሉት መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት የሚያስችሉ የማህበራዊ አገልግሎት እንዲዳረሱ በማድረጉ በኩል አስተዋፅኦ አድርጓል። በመሆኑም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እ.ኤ.አ በ20015 ታዳጊ ሀገራት እንዲያሳኩት ያስቀመጠውን የሚሊኒየሙን የልማት ግብ ከሚያሳኩት ጥቂት ሀገራት ውሰጥ ኢትዮጵያ በግንባር ቀደምትነት የምትጠቀስ ለመሆን በቅታለች፡፡

አንድ አብነትን ላንሳ–የጤና ዘርፉን ዕመርታ። ኢትዮጵያ ከምዕተ-ዓመቱ የልማት ግብ አንዱ የሆነውንና ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት ሞትን ለመቀነስ የተቀመጠውን ግብ በማሳካት ረገድ፤ እ.ኤ.አ. በ1990 ዓ.ም. ከአንድ ሺ ህፃናት ውስጥ 204 የነበረውን የሞት መጠን እ.ኤ.አ. በ2012 ዓ.ም. ወደ 68 ዝቅ ማድረግ ችላለች። ይህም በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ የ67 በመቶ ለውጥ ያሳየ ወይም የሞት መጠኑን በሁለት ሶስተኛ የቀነሰ ነው። በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስር የሚገኙት እንደ የመንግስታቱ ድርጅት የህፃናት ፈንድን (UNICEF)፣ የዓለም አቀፉ የምግብ ድርጅትን (WHO)፣ የዓለም ባንክ ቡድንን (World Bank Group) የመሳሰሉ ተቋማት ባወጡት ተመሳሳይ ሪፖርት ላይ እንደተጠቆመው፤ ባለፉት 22 ዓመታት የተከናወነው ይህ የሀገራችን ውጤታማ ተግባር ከልማት ግቡ ሶስት ዓመት በፊት አስቀድሞ የተሳካ መሆኑ ተገልጿል።

እርግጥ ለዚህ ውጤት መገኘት የአንሳውን ድርሻ የሚወስዱት ልማታዊው መንግስትና ታታሪው የሀገራችን ህዝብ ናቸው– ሁለቱም ተቀናጅተውና እጅ ለእጅ ተያይዘው በመስራታቸው ይህን መሰል ወርቃማ ድል ማስመዝገብ ችለዋልና። ውጤቱ በአንድ በኩል ለሀገራችንና ህዝቦችና ለወዳጆቿ ደስታ ሲሆን፤ ጠላቶቿንና ‘ልማት የለም’ እያሉ የሚያላዝኑ ‘ጥቁር ቀለም ቀቢዎችን’ አንገት የሚያስደፉ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ “የተለጠጠ ነው” እየተባለ የሚነገርለት የአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ሊደረስበት የሚችል መሆኑን የሚያመላክት ይመስለኛል። ታዲያ እዚህ ላይ ‘የዚህ አኩሪ ውጤት መገኘት ምስጢሩ ምንድነው?’ ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። ለምላሹ ግን ሩቅ መሄድ የሚያሻን አይመስለኝም።

በእኔ እምነት የዚህ ውጤት መገኘት በርካታ ጉዳዩች ሊገለፁ ይችላሉ። ከእነዚህ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የሚገለፅ የፖለቲካ ቁርጠኝነት፣ በጤናው መስክ ያለው ጠንካራ አመራር፣ የባለ ድርሻ አካላት ውጤታማ አደረጃጀት እንዲሁም የአጠቃላይ ማህበረሰቡ በተመሳሳይ ልማታዊ አስተሳሰብ እየተመራ የያዘው ቁርጠኛ አቋምና ያደረገው ተሳትፎ ተጠቃሽ ናቸው። እርግጥ መንግሥት አምራች ዜጋን ለመፍጠር የሚሠራው ጤነኛ ዜጋ ከመፍጠር ሥራ ተነጥሎ አይታይም በሚል እምነት የጤናን ፕሮግራሞች መተግበሩ ሌላኛው ምክንያት ነው። ከዚህ በተጨማሪም መንግሥት የጤናን ፕሮግራም ሰፊውን የገጠርና የከተማ ህዝብ ለማገልገል የተቃኘና በመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ላይ አትኩሮ በመስራቱ እንዲሁም ሕዝቡን ተጠቃሚ ማድረጉ ነው፡፡

የመሠረተ ጤና አገልግሎቱ ራሱ መከላከልን ማዕከል ያደረገ በመሆኑ መላው ህዝብ ራሱን መሠረት ያደረገ ጤንነትና የማረጋገጥ ስርዓት ዘርግቶ በባለሙያዎች እየታገዘ ተግባራዊ በማድረግ ተጠቃሚ እየተደረገ ነው፡፡ በየቀበሌው ለ5000 ሰው አንድ የጤና ኬላና ሁለት ሴት የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን መድቧል። ለ25ሺ ሰዎች አንድ የጤና ጣቢያ ሂሳብ የጤና ጣቢያዎችን ገንብቷል። የሰው ኃይልና የቁሳቁስ አቅርቦት በማሟላት ረገድም በባለሙያዎቹ ዘንድ የአገልጋይነት አመለካከት ከመፍጠር በተጓዳኝ በአርብቶ አደሩ አካባቢ እንዲስፋፋ በማድረጉና በዚህም በዘርፉ የምዕተ ዓመቱን ግቦች ለማሳካት ውጤታማ ስራ ማከናወኑ የስኬቱ ተጠቃሽ ምክንያት ይመስለኛል፡፡ በያዝነው ዓመትም ልክ እንደ ሌሎቹ ዓመታት ሁሉ ሀገራችን የ11 ነጥብ አራት በመቶ ዕድገት እንደምታስመዘግብ የኢፌዴሪ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር አቶ ሶፊያን አህመድ በቅርቡ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መግለፃቸውም የአምስት ዓመቱ የልማት ዕቅድ ተደራሽ መሆኑን የሚያመላክት ነው።

እንደሚታወቀው የሀገራችንን ምጣኔ ሃብት እየመራ ያለው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ነው፡፡ ይህም ግብርናውን በፍጥነት በማሳደግ ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን ሽግግር እውን ለማድረግ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ ታዲያ ግብርናው በፈጠረው ምቹ ሁኔታ በመጠቀም ኢትዮጵያችንን በኢንዱስትሪ የበለፀገች ለማድግና መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማቀላቀል፣ መንግስት በነደፈው የአምስት ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሰፊ ርብርብ እያደረገ ነው፡፡ እንዳለፉት አስር ዓመታት ሁሉ በቀጣዩቹ ዓመታትም በሀገሪቱ የተቀጣጠለውን የዕድገት ችቦ ይበልጥ በማድመቅ።

## የዕድገቱ ውጤት

ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው ሀገራችን ያስመዘገበችው ልማታዊ ዕድገት ዓለም በፋይናንስ ቀውስ በተመታችት ወቅት የተገኘ ነው። በተለይም የኒዮ-ሊበራል የፋይናንስ ተቋማት ከፍተኛ ኪሳራ ሲደርስባቸውና መንግስታቸውም ከሚከተለው ርዕዮተ-ዓለም አፈንግጦ ድጎማ እስከማድረግ በደረሰበት በዚያን ወቅት የሀገራችን ምጣኔ ሃብት አንዳችም መንጋደድ ሳያሳይ መቀጠሉ መንግስት የተከተላቸው ፖሊሲዎች ምን ያህል አዋጪዎችና በውጤታቸውም ህዝቡንም በየደረጃው ተጠቃሚ ያደረጉ መሆናቸውን የሚያሳዩ ዕውነታዎች ናቸው።

በመሆኑም ይህ ዓለም በተመታችው የገንዘብ ቀውስ ውሽንፍር ሳይበገር ህዝቡን የዕድገት ውጤቱ ተጠቃሚ ያደረገው የመንግስታችን አቅጣጫ ዛሬ ላይ የልማቱ አንድ አካል የሆነውን የመንግስት ሰራተኛ የኑሮ ሁኔታ አቅም በፈቀደ መጠን ለመለወጥ የታለመ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። የደመወዝ ጭማሪውና የማትጊያ ጥቅማ ጥቅሞቹ ከዚሁ አኳያ መታየት ያለባቸው ይመስለኛል። ታዲያ ይህ መንግስት ለሰራተኛው ክፍል ያደረገው ተጠቃሚነትን ከፍ የሚያደርግ አካሄድ የታቀዱ ትልሞች እንዲሳኩ እንዲሁም ሕዝቡ ከመንግሥት ማግኘት የሚገባውን ልማታዊ ትሩፋቶችን እንዲያገኝ የሚያደርጉ ናቸው። ይሁንና የመንግስት ሰራተኛው ከዕድገቱ ጋር ተከትሎ የደመወዝ ጭማሪ ሲደረግለት አንዳንድ ስግብግብ ነጋዴዎች የዋጋ ጭማሪ ሊያደርጉ ይችላሉ። ምንም እንኳን ጭማሪው በዋጋ ግሽበት ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ እንዳያስከትል በመንግስት በኩል ቀደም ሲል ጥናት የተደረገበት ጉዳይ ቢሆንም፤ እነዚህን ስግብግብ ነጋዴዎች መከላከልና መቆጣጠር የእያንዳንዱ ዜጋ ግዴታና ሃለፊነት መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ስለሆነም ሀገራችን ባስመዘገበችው ልማታዊ ዕድገት ውጤት ወደፊትም ግለቱን ጠብቆ እንዲሄድ እነዚህን ወገኖች እየተከታተሉ ለሚመለከተው አካል ጥቆማ በመስጠት ሁላችንም የቡላችንን ሚና መጫወት ይኖርብናል ባይ ነኝ። ቸር እንሰንብት።